# የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ፤ ተጓዳኝ የሁለትዮሽ ውይይቶችና አንድምታቸው

ብ. ነጋሽ

28ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ የህብረቱ መቀመጫ በሆነችው ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ተካሂዶ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ሲሆን እንደኖረው በሰላም ተጠናቅቋል። ከ40 በላይ የአፍሪካ አገራትና የሌሎች አገራት መሪዎች፤ እንዲሁም የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መሪዎችና ተወካዮች የተሳተፉበት የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ በበርካታ አህጉራዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔዎችን ማሳለፉ ይታወቃል። ከዚህ በተጓዳኝ የአገራት መሪዎች ተገናኝተው በየአገራቸው የሁለትዮሽ ጉዳዮች ላይ ተመካክረዋል። ተግባብተዋል፤ ተስማምተዋል። የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ከዋናው የጉባኤው አጀንዳዎች በተጓዳኝ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መሪዎች በአንድ ቦታ የመገናኘት እድል ስለሚያገኙ አገራት የሁለትዮሽ ጉዳያቸውን የሚወያዩበትና የሚስማሙበት አመቺ አጋጣሚ ይፈጥራል። እንዲህ ዓይነቱን አጋጣሚ ከተጠቀሙት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ነበረች።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ለጉባኤው አዲስ አበባ ከተገኙ መሪዎች ጋር የሁለትዮሽ ውይይት አድርገዋል። ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ጋር  ውይይትና ስምምነት ካደረጉት መሪዎች መካከል የግብጽ ፕሬዝዳንት አብዱል ፈታህ አልሲሲ፣ የደቡብ ሱዳን ፕሬዝዳንት ሳለቫኬር ማያርዲት፣ የሱዳን ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ሃሰን አልበሽር፣ የሩዋንዳ ፕሬዝዳንት ፖል ካጋሚ፣ የላይቤርያ ፕሬዝዳንት ኤለን ጆንሰን፣ የኡጋንዳው ፕሬዝዳንት ዩዌሪ ሙሲቪኒ፣ የጊኒው ፕሬዝዳንት አልፋ ኮንዴ፣ የጅቡቲው ፕሬዝዳንት ኢስማኢል ኡመር ጊሌ፣ የአልጄሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር አብዱል ማሊክ ሴላል ተጠቃሾቹ ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ከመሪዎቹ ጋር ባደረጉት የሁለትዮሽ ውይይት የተነጋገሩባቸውን ጉዳዮችና የደረሱባቸውን መግባበቶች በመጠኑ እንመልከት።

ከሩዋንዳው ኘሬዝዳንት ፓል ካጋሚና ከላይቤርያዋ ኘሬዝዳንት ኤለን ጆንሰን  ጋር የአገራቱን ግንኙነት ማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መክረዋል። የሁለቱም አገራት መሪዎች ከኢትዮጵያ ጋር በግብርና፤ በኢንዱስትሪ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ዘርፍ ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከር እንደሚፈልጉ አመልክተዋል። የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ አገራቸው ከሩዋንዳና ከላይቤሪያ ጋር በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች፤ እንዲሁም  በአህጉራዊ እና አለማቀፍዊ ጉዳዮች ላይ ተባብራ መስራት እንደምትፈልግ ማረጋገጣቸውን ውይይቱን የተከታተሉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አቶ ተወልደ ሙሉጌታ ለመገናኛ ብዙሃን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ከጊኒው ፕሬዚዳንት አልፋ ኮንዴም ጋር አገራቱ ቀደም ሲል የደረሱባቸው ስምምነቶች ተፈፃሚ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ዙሪያ መክረዋል። ባለፈው ዓመት ሚያዚያ ወር ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጊኒን መጎብኘታቸው ይታወሳል። በዚህ ወቅት ሁለቱ አገራት በትብብር ለመስራት ሃያ ያህል ስምምነቶች ተፈራርመው ነበር። በሰሞኑም የሁለትዮሽ ስምምነነቶቹን ተፈፃሚ ለማድረግ እንደሚሰሩ መግባባት ላይ ደርሰዋል። የጊኒ መንግስት ከኢትዮጵያ የግብርና ተሞክሮ ለመጋራት እንደሚፈልግ በገለጸው መሰረት ለዚህ ተግባር እንዲረዳ የአገሪቱ የግብርና ሚኒስትር ከፕሬዝዳንቱ ጋር ወደአዲስ አበባ መጥተው ነበር። የግብርና ሚኒስትሩ በአዲስ አበባ ቆይታቸው ልምድ የሚቀስሙበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸው እንደነበረም ታውቋል።

ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለ ማርያም ከሱዳኑ ፕሬዝዳንት ኦመር ሃሰን አልበሽር ጋርም በሁለትዮሽ አገራዊ የጋራ ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል። በውይይቱ ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር ያላትን የቆየና ታሪካዊ ግንኙነት በንግድ እና በኢኮኖሚ  ዘርፍ ለማጠናከር ዝግጁ መሆኗን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ገልፀዋል። ሁለቱ አገራት ረጅም ድንበር የሚጋሩና ተመሳሳይ ባህል ያላቸው በመሆናቸው፣ በኢኮኖሚ እና በንግድ ዘርፎች ጠንካራ  ትስስር መፍጠር ይገባል የሚል አቋም እንዳላቸውም ገልጸዋል። ፕሬዝዳንት አልበሽር በውይይቱ  ወቅት አገራቸው በንግድና በኢኮኖሚ ትስስር ዘርፍ  ከኢትዮጵያ  ጋር  በጋራ  መስራት እንደምትፈልግም ተናግረዋል።

ከላይ የተገለጹት ከመሪዎች ጋር የተደረጉ የሁለትዮሽ ውይይቶችና መግባባቶች ለዲፕሎማሲ ወግ ያህል ብቻ የተደረጉ አይደሉም። ከዚህ በላይ ፋይዳ አላቸው። ይልቁንም፤ በአገራቱ መካከል ያለውን በበጎ የመፈላለግ፣ የመጠቃቀም ግንኙነት የመመስረት፣ የመደጋገፍ፣ . . . ፍላጎት ያሳያል። ይህን በኢትዮጵያ በኩል ሆነን ስንመለከተው አገራቱ ከኢትዮጵያ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ፍላጎት ያላቸው መሆኑን፣ የዚህ ፍላጎት መነሻ ደግሞ አገሪቱ በሰላምና በኢኮኖሚ ትብብርና ግንኙነት ጠቅማ የመጠቀም አቅም ስላላት መሆኑን ያመለክታል። እናም የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ በማጉላት ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ከደቡብ ሱዳን ፕሬዝዳንት ሳልቫኬርና ከግብጹ አልሲሲ ጋር ያደረጓቸው የሁለትዮሽ ውይይቶች ከላይ ከተገሉት የተለየ ትኩረት የሳቡ ነበሩ። በተለይ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፤ የደቡብ ሱዳንን በተመለከተ በተለይ በውጭ አገር የሚገኙ ማህበራዊ ሚዲያዎች ደቡብ ሱዳን ከግብፅ ጋር ኢትዮጵያን የሚጎዳ ስምምነት አድርጋለች፣ ይህም ኢትዮጵያን አስፈርቷታል። የሚል ወሬ ሲነዙ መቆየታቸው ነው ትኩረት እንዲስብ ያደረገው፤ የግብጹን በተመለከተ፣ እንደተለመደው ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ጋር በተያያዘ ግብጽ ልትይዝ የምትችለውን አቋም መነሻ በማድረግና በተለይ ባለፈው ዓመት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች አጋጥሞ ከነበረው ሁከት ጀርባ የግብጽ ተቋማት እጅ እንደነበረበት ያመለክቱ መረጃዎች የነበሩ መሆናቸው ነው። ያም ሆነ ይህ፤ መሪዎቹ የሁለትዮሽ ውይይት አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ከደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫኪር ማያርዲት ጋር የተወያዩት በጽህፈት ቤታቸው ነበር። የውይይታቸው አንዱ አጀንዳ በቅርቡ በሁለቱ አገሮች ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ላይ ችግር ተፈጥሯል በሚል ሲናፈስ የነበረው ጉዳይ ነበር። ከውይይቱ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት መግለጫ አሉባልታው ከእውነት የራቀ ነበር ብለዋል። የአገራቱን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር በመንገድ መሰረተ ልማት የማስተሳሰር፣ የነዳጅ ማጣሪያ፣ ማጋዟዣ መስመርና መሰል የልማት ፕሮጀክቶችን በጋራ ለመሥራት መስማማታቸውንም ገልጸዋል። ፕሬዚዳንት ሳልቫኪር በቅርቡ ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋብዘዋቸዋል። ሳልቫኬርም ግብዣውን ተቀብለዋል። በጉብኝታቸው አገራቱ መሠረታዊ የሆኑ ስምምነቶች እንደሚፈራረሙ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ገልጸዋል።

የደቡብ ሱዳኑ ፕሬዚዳንት ሳልቫኪር ማያርዲትም በቅርቡ ስለተናፈሰው ወሬ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ጋር በግልጽ መወያየታቸውንና የተባለው ሁሉ ከእውነት የራቀ ወሬ መሆኑን ተናግረዋል። በአገራቱ መካከል ምንም ዓይነት ወሬ ቢናፈስ መሪዎቹ ተቀራርበው በመነጋገር ግንኙነታቸውን ይበልጥ ማጠናከር እንደሚችሉም አመልክተዋል።

መሪዎቹ ስለ አፍሪካ ቀንድ አካባቢ፤ እንዲሁም በደቡብ ሱዳን ሠላም ማስፈን በሚቻልበት ጉዳይ ላይም ተወያይተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ኢትዮጵያ ለደቡብ ሱዳን ሠላምና መረጋጋት ከፍተኛ እገዛ እያደረገች እንደምትገኝና በቀጣይም ይህንኑ አጠናክራ እንደምትቀጥል ማረጋገጣቸውን ገልጸዋል። ደቡብ ሱዳን በአስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ ሆና እንኳን ኢትዮጵያ አልተለየቻትም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም፤ ይህም በሁለቱ አገሮች መካከል ጠንካራ ግንኙነት መኖሩን እንደሚያሳይ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ከግብጹ ፕሬዚዳንት አል ሲሲ ጋር ባካሄዱት የሁለትዮሽ ውይይት አምስት ነጥቦችን አንስተው ተወያይተዋል። ሁለቱ መሪዎች በአገራቱ መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጠናከር እስካሁን የተገኙ መልካም ዲፕሎማሲያዊ ድሎችን ለማጉላት እንደሚጠቅምና የሁለትዮሽ መተማመን ለመፍጠር እንደሚያግዝ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል። ሁለትዮሽ ቀጠናዊ የትብብር መስኮችን ማስፋት እና ማጠናከር፤ በተለይም በፖለቲካ፣ በሰላምና ፀጥታ፣ በኢኮኖሚ ዘርፍ ያሉ ትብብሮችን ማጉላት እንደሚገባ፣ ሁለትዮሽ ግንኙነትና ወንድማማችነትን የሚጎዳ ማንኛውንም አይነት ክስተት መቆጣጠርና መገደብ እንደሚገባ ከስምምነት ላይ ደርሰዋል።

መሪዎቹ ታላቁን የህዳሴ ግድብ አስመልክቶ የሶስትዮሽ የቴክኒክ ኮሚቴ ውይይቶችን እየተከታተሉ መሆኑን አስታውቀው። ግድቡን አስመልክቶ ያላቸውን  በትብብር የመስራት ቁርጠኝነት ለማደስ ተስማምተዋል። የመረጃ ልውውጥን ለማሳደግ፣ የሁለትዮሽ ግንኙነትንና የጋራ ጉዳይ በሆኑ ቀጠናዊና አለም ዓቀፋዊ ጉዳዮች በመሪዎችና በተቋማት ደረጃ ተከታታይነት ያለው ምክክር ለማካሄድም ተስማምተዋል።

የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ማጎለበት፣  በህዝቦች መካከል ያለውን መተማመን ማበልጸግ እንደሚያስፈልግ አንስተው፤ ለዚህም የመገናኛ ብዙሃን ወሳኝ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል በሚል ተስማምተዋል። ሁለቱ መሪዎች በቋሚነት በተለያየ ጊዜ በሁለቱ አገራት ጉብኝት እንደሚያደርጉም መግባባት ላይ ደርሰዋል። ፕሬዚዳንት አል ሲሲ  ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም በቅርቡ ግብጽን እንዲጎበኙ ጋብዘዋቸዋል።

እንግዲህ በደቡብ ሰዳንና በኢትዮጵያ፣ እንዲሁም በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት መሰናከል ገጥሞታል ሲባል የነበረ ቢሆንም፣ የመሪዎቹ የሁለትዮሽ ውይይት ቢያንስ ሁለቱም ወገኖች አለመግባባቱን እንደማይፈልጉት አመላክቷል። ይህ ደግሞ በመጠቃቀም ላይ ለተመሰረተ መልካም ግንኙነት መሰረት ነው።

በአጠቃላይ፤ ከ28ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ በተጓዳኝ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ከመጡ መሪዎች ጋር ያደረጉት የሁለትዮች ውይይት፣ ኢትዮጵያ በሌሎች አገራት ዘንድ በመጠቃቀም ላይ ለተመሰረተ ግንኙነት ያላትን ተፈላጊነት ያሳያል። የደበዘዙና የደበዘዙ የሚመስሉ ግንኙነቶችንም ማደስ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።